ግርማዊ ፡ ሆይ ።

በምናብብበትና ፡ በምንበለጽግባቸው ፡ የወዳጅነት ፡ መንፈስና ፡ የጋራ ፡ ሐሳቦች ፡ ግብ ፤ ለግርማዊነትዎና ፡ ለግርማዊት ፡ ጤና ፤ ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሀብትና ፡ ደስታ ፡ ጽዋዬን ፡ አነሣለሁ ።

* * *

ለ) የግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንግግር ።

ግርማዊት ፡ ሆይ ።

ግርማዊትነትዎ ፡ በተናገሩዋቸው ፡ መልካም ፡ የእንግድነት ፡ አቀባበል ፡ በተመላባቸው ፡ ቃሎችና ፡ ስለኔም ፡ ስለራሴ ፡ በገለጹዋቸው ፡ የልግስና ፡ ስሜቶች ፡ ልቤ ፡ በጥልቅ ፡ ተነክቷል ። ምንም ፡ እንኳ ፡ ይህችን ፡ የተዋበች ፡ አገርዎን ፡ የረገጥሁት ፡ ከጥቂት ፡ ሰዓቶች ፡ በፊት ፡ ቢሆን ፡ ግርማዊትነትዎ ፡ የተናገሩዋቸው ፡ ቃሎች ፡ የዛሬ ፡ ፲፬ ፡ ዓመት ፡ ከዚህ ፡ አገር ፡ ከመሄዴ ፡ በፊት ፡ የተደረገልኝን ፡ አስተያየት ፡ የሚያሳስቡኝ ፡ ሆነዋል ።

ወደ ፡ ግርማዊትነትዎ ፡ አገር ፡ ስመጣ ፡ ዛሬ ፡ መጀመሪያ ፡ ጊዜዬ ፡ አይደለም ። የዛሬ ፡ ሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ይህን ፡ አገር ፡ ለመጐብኘት ፡ ስመጣ ፡ ወደዚህ ፡ ታላቅ ፡ ከተማ ፡ እንደ፡ደረስሁ ፡ በአፊሲዬል ፡ የተቀበሉኝ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የዮርክ ፡ መስፍን ፤ ኋላ ፡ ግን ፡ ጆርጅ ፡ ፮ኛው ፡ የነበሩት ፡ ግርማዊ ፡ አባትዎ ፡ ነበሩ ። የተወደዱት ፡ ንጉሥ ፡ ያደረጉልኝ ፡ የወዳጅነት ፡ አቀባበል ፡ ከንጉሣዊ ፡ ባሕሪያቸው ፡ ጋራ ፡ የተዋሐደ ፡ መሆኑ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ትዝ ፡ ይለኛል ።

ባለፉት ፡ ሠላሳ ፡ ዓመቶች ውስጥ ፡ በአገሬ ፡ ላይ ፡ ደርሶ ፡ የነበረው ፡ መሪር ፡ የሆነ ፡ ረጅም ፡ የመከራ ፡ ጊዜያትና ፡ እኔም ፡ ራሴ ፡ ባሳለፍሁት ፡ የስደት ፡ ዘመን ፡ ሲያጽናናን ፡ የቈየው ፡ የንጉሣዊ ፡ ቤተ ፡ ሰብዎ ፡ መልካም ፡ አስተያየትና ፡ የታላቁ ፡ የእንግሊዝ ፡ ሕዝብ ፡ ወዳጅነትና ፡ እንግዳ፡ ተቀባይነት ፡ ነው ። እኔና ፡ ሕዝቤ ፡ ብቻችንን ፡ ያለ፡ አንድ ፡ ረዳት ፡ ባደረግነው ፡ ተጋድሎ ፡ ደጋፊያችን፡የነበረው ፡ የእንግሊዝ ፡ ንጉሣዊ ፡ ቤተ ፡ ሰብና ፡ የእንግሊዝ ፡ ሕዝብ ፡ ፍቅር ፡ ብቻ ፡ ነበር ። ይህ ፡ ወዳጅነትና ፡ ታማኝነት ፡ የኛን ፡ የማይጠፋ ፡ ውለታና ፡ ወዳጅነት ፡ አትርፎዋል ።

የግርማዊትነትዎ፡ እርዳታና ፡ የልጆቻቸው ፡ ደም ፡ ከልጆቻችን፡ደም ፡ ጋራ ፡ በኢትዮጵያ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ያፈሰሰው ፡ የእንግሊዝ ፡ ሕዝብ ፡ ታማኝነት ፡ በሁለቱ ፡ አገሮቻችን ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ወዳጅነትና ፡ መተሳሰብ ፡ እንደ ፡ ተቀደሰ ፡ አደራ ፡ ተጠብቆ ፡ እንዲኖር ፡ አድርጎታል ።

እነዚሁም ፡ የእንግሊዝ ፡ ጀግኖች ፡ በአገራቸው ፡ መሬትና ፡ ደግሞ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ነፃነት ፡ ለማስመለስ ፡ በአገራችን ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ የፈጸሙዋቸው ፡ ክብር ፡ የመላባቸው ፡ ተጋድሎዎች ፡ ናቸው ።

ምንም ፡ እንኳ ፡ የታሪኩ ፡ ዘመን ፡ ጎዘንና ፡ መሥዋዕትነትን ፡ የሥራ ፡ ፍሬንና ፡ ክብርን ፡ እያፈራረቀ፡ ያስገኘ ፡ ቢሆን ፡ መጨረሻው ፡ ዘመን ፡ ብሩህና ፡ ታላቅ ፡ ተስፋ ፡ ያለው ፡ ለመሆኑ ፡ ጸጋ ፡ የተሰጣቸው ፡ የወጣቷ ፡ ንግሥት ፡ እጅግ ፡ ከፍ ፡ ባለው ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ መቀመጥ፡ የሚበቃ ፡ ምልክት ፡ ነው ።

ግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ በሚያሳዝን ፡ አጋጣሚ ፡ በጤናዋ ፡ ምክንያት ፡ በዚህ ፡ ለመገኘት ፡ ለመምጣት ፡ ባለመቻሏ ፡ እጅግ ፡ ታዝናለች ፤ ይህንም ፡ ጎዘናን ፡ ለግርማዊት ፡ ንግሥት ፡ እንድገልጽላት ፡ ለምናኖለች ።

በታላቅ ፡ አክብሮትና ፡ አድናቆት ፡ ለምንመለከታቸው ፡ ለግርማዊት ፡ ንግሥት ፡ ጤና ፡ ጽዋችንን ፡ እናነሣለን ።

432

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ጥቅምት ፡ ፭ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፸፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በ፮ ፡ ሰዓት ፡ ከክብር ፡ ተስታዮቻቸው ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ጊልድ ፡ ሆል ፡ ሄዱ ። የሎንዶን ፡ ከንቲባ ፡ በጊልድ ፡ ሆል ፡ አዳራሽ፡ ስለ፡ ግርማዊነታቸው ፡ ክብር ፡ ባደረጉት ፡ ግብዣ ፡ ላይ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የተናገሩት ፡ ቃል ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ነው ።

የተከበሩ ፡ ከንቲባ ።

የእንግሊዝን ፡ አገር ፡ በአፊሲዬል ፡ ለመጐብኘት ፡ በመጣሁበት ፡ በዚህ ፡ ቀን ፡ ስለ ፡ ተደረገልኝ ፡ መልካም ፡ አቀባበል ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ ደስታ ፡ ተሰምቶኛል ። ከአገሬ ፡ በወጣሁበት ፡ ዘመን ፡ በእንግሊዝ ፡ ሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ መልካም ፡ አቀበባል ፡ አግኝቼ ፡ ከቈየሁባቸው ፡ ከነዚያ ፡

የችግር ፡ ቀኖች ፡ ጀምሮ ፡ ስለዚህ ፡ አገር ፡ ያለኝ ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ የወዳ ጅነት ፡ ስሜት ፡ መቼውንም ፡ ቢሆን ፡ ከአሳቤ ፡ አልተለየም ።

ኢትዮጵያም ፡ እንደ ፡ ታላቂቷ ፡ ብሪታኒያ ፡ ሲያያዝ ፡ የመጣ ፡ ረጅም ፡ ታሪክ ፡ አላት ። የእናንተ ፡ ንጉሥ ፡ ኤግበርት ፡ በነገሠበት ፡ ዘመን ፡ ኢትዮጵያን ፡ ይገዛ ፡ የነበረው ፡ ንጉሥ ፤ ከእኛም ፡ ትውልደ ፡ መንግሥት ፡ ከቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ጀምሮ ፡ ሲቈጠር ፡ ሙቶ ፡ አምሳ ፡ ሁለተኛው ፡ ንጉሥ ፡ አጼ ፡ ውድም ፡ አስፈሬ ፡ ነበር ። እኛም ፡ እንደናንተ በቅንአት ፡ መንፈስ ፡ እየተከላከልን ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ያለንን ፡ ነፃነት ፡ ጠብቀን ፡ አቈይተናል ። ለብቻ ፡ የመኖር ፡ ዘዴ ፡ አለመጥቀሙን ፡ በመ መልከት ፡ አገራችን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ጥቂት ፡ በጥቂት ፡ እንድትታወቅና ፡ ለዓለም ፡ መገናኛዋ ፡ የተከፈተ ፡ እንዲሆን ፡ አደረግን ፤ ለዚህም ፡ የእና ንተ ፡ የእንግሊዝ ፡ ወዳጆቻችን ፡ እርዳታ ፡ አገልግሏል ።

ብዙ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ኢትዮጵያን ፡ ጐብኝተዋል ። ከነር ሱም ፡ አንዳንዶቹ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ከመኖራቸው ፡ የተነሣ ፡ በአገሪቱ ፡ ውስጥ ፡ ከፍ ፡ ያለና ፡ የሚጠቅም ፡ ትምህርት ፡ ለመተው ፡ ችለ ዋል ። የእንግሊዝ ፡ ተወላጆችም ፡ በአገሪቱ ፡ ውስጥ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ባይቈዩ ፤ ኢትዮጵያን ፡ ከዓለም ፡ ጋራ ፡ ለማስተዋወቅ ፡ ዕድሉ ፡ የነርሱ ፡ ሆኗል ። በዚህም ፡ ረገድ ፡ ብሩስን ፡ የሚተካከለው ፡ የሚገኝ ፡ አይመስልም ። በየጊዜው ፡ እየተከታተሉ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለመጡት ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎችና ፡ ደራሲዎች ፡ ብሩስ ፡ ቀዳሚ ፡ መሆኑ ንና ፤ ደግሞ ፡ አውሮፓዎችና ፡ ምዕራባዊው ፡ ዓለም ፡ ኢትዮጵያን ፡ በተ ጣራ ፡ አኳኋን ፡ ለማወቅ ፡ የቻሉት ፡ በነዚህ ፡ ጐብኝዎችና ፡ ደራሲዎች ፡ እርዳታ ፡ መሆኑ የተገለጠ ፡ ነው ። የቤክና ፡ የሐሪስ ፡ በመጨረሻም ፡ የፕ ላውደን ፡ ስም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ የታወቀ ፡ ሆኖ ፡ ይኖራል ።

ስለዚህ ፡ ከአውሮፓ ፡ ጋራ ፡ የተደረገው ፡ ዘመናዊ ፡ ውል ፡ በኢት ዮጵያና ፡ በታላቂቱ ፡ ብሪታኒያ ፡ መካከል ፡ በጎዳር ፡ ፮ ፡ ቀን ፡ ፲፰፻፬፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተፈርሞ ፡ መገኘቱ ፡ በአግባብ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ። በእውነትም ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከማናቸውም ፡ ሌላ ፡ አገር ፡ ይልቅ ፡ ከታላቂቱ ፡ ብሪታኒያ ፡ ጋራ ፡ የተፈራረመቻቸው ፡ ውሎችና ፡ ስምምነቶች ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ።

ኢትዮጵያ ፡ ከዓለም ፡ ጋራ ፡ ያላት ፡ መገናኛ ፡ ክፍት ፡ መሆኑን ፡ በመግለጥ ፡ አብዛኛውን ፡ የረዱንን ፡ የእንግሊዝ ፡ ደራሲዎችንና ፡ አገር ፡ ጐብኝዎችን ፡ እያመሰገንን ፤ ከዚያ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ በሁለቱ ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ የጥቅም ፡ ሙተሳሰር ፡ እያደገ ፡ ሲመጣ ፡ እስከዚህ ፡ ደርሶ ፡ ዛሬ ፡ ከመቼውም ፡ ይልቅ ፡ በበለጠ ፡ አኳኋን ፡ የተቀራረበ ፡ መሆኑን ፡ ስንመለከት ፡ ደስ ፡ ይለናል ።

ይኸውም ፡ መቀራረብ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ነፃነት ፡ ለማስመለስ ፡ የእንግ ሊዝ ፡ ጀግኖች ፡ ደም ፡ በፈሰሰበት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ድል ፡ ባስገኘው ፡ የጦር ፡ ጓደኝነት ፡ ጕልህ ፡ ሆኖ ፡ ታይቷል ።

በሁለቱ ፡ አገሮቻችን ፡ መካከል ፡ የሚገኘው ፡ ግንኙነት ፡ ቢጋራ ፡ ጥቅም ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፤ ተወዳዳሪ ፡ በሌለው ፡ እርምጃ ፡ በሚያደር ጉት ፡ በፖለቲካ ፡ ድርጅቶቻችሁ ፡ ላይ፡የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ባሳደረው ፡ አድናቆት ፡ ጭምር ፡ የተመሠረተ ፡ ነው ፤ የፖለቲካና ፡ የሃይማኖት ፡ ነፃ ነት ፡ በጽኑ ፡ ተመሥርቶ ፡ እድገትን ፡ እያገኘ ፡ ይሄድ ፡ ዘንድ ፡ በማበረ ታታት ፡ ተመሳሳይ ፡ የሌለው ፡ ምሳሌ ፡ ለዓለም ፡ ሰጥታችኋል ። እኛም ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥታችንን፡በዘመናዊው ፡ አኳኋን ፡ ስናቋቁም ፡ ለነበረብን ፡ ድካም ፡ የእንግሊዝ ፡ ተወላጅ ፡ የሆኑ ፡ ኤክስፔርቶች ፡ በተ ለይም ፡ የሕግ ፡ ዐዋቂዎችና ፡ ዳኞች ፡ የፈጸሟቸው ፡ ሥራዎች ፡ በኢት ዮጵያ ፡ የፖለቲካዊና ፡ የማኅበራዊ ፡ ድርጅቶች፡ ላይ ፡ የማይረሳ ፡ ምሳሌ ፡ ትተዋል ። ዛሬ ፡ የእንግሊዝን ፡ ቋንቋ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥቲ ፡ ግዛታችን ፡ ሁለተኛ ፡ የትምህርት ፡ ቋንቋ ፡ ስላደረግነው ፡ በከፍተኞች ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ሁሉ ፡ ትምህርት ፡ ይሰጥበታል ።

ከዚህ ፡ በቀር ፡ ተወዳዳሪ ፡ በሌለው ፡ አኳኋን ፡ ባህልና ፡ መንፈሱን ፡ በማሳደግ ፡ የእንግሊዝ ፡ ሕዝብ፡ ስለፈጸመው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ተግባር ፡ የኢ ትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ የእንግሊዝን ፡ ዘውድ ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ የአክብ ሮት ፡ አስተያየት ፡ እንደ ፡ ሰጠው ፡ ነው ።

የኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ በ፲፯ኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ መጀመሪያ ፡ ላይ ፡ ከእንግሊዝ ፡ ንጉሥ ፡ ከኪንግ ፡ ጀምስ ፡ ፩ኛ ፡ ጋራ ፡ ይጻጻፍ ፡ ነበር ። ባለ ፈው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ መጨረሻ ፡ አቅራቢያ ፡ በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ የሞ ተው ፡ የመስፍን ፡ ዓለማየሁ ፡ ዐፅም ፡ በዊንድሶር ፡ ካሉት ፡ መቃብሮች ፡

ብአንደኛው ፡ ውስጥ ፡ ይገኛል ። ዛሬም ፡ በእንግሊዝ ፡ ዘውድ ፡ ያለንን ፡ አድናቆት ፡ በመከተል ፡ ትምህርታቸውንና ፡ ዕውቀታቸውን ፡ እንዲያስፋፉ ፡ የንጉሣዊ ፡ ቤተ ፡ ሰባችንን ፡ ጭምር ፡ ወደ ፡ እንግሊዝ ፡ አገር ፡ ለትምህርት ፡ ልከናል ። ከዚህ ፡ በቀር ፡ በሁለቱ ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ አሁን ፡ ብሙሉ ፡ ተስፋፍቶ ፡ የሚገኘውን ፡ የመረዳዳትና ፡ የጋራ ፡ መግባባትን ፡ መተሳሰሪያ ፡ የበለጠ ፡ ለማጠንከር ፡ የዛሬ ፡ ሠላሳ ፡ ዓመት ፡ እኔው ፡ ራሴ ፡ ወደዚህ ፡ አገር ፡ መጣሁ

ታላቂቱ ፡ ብሪታኒያ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ንግድ ፡ ጕዳይና ፡ በሌላም ፡ ሥራ ፡ ዐይነተኛ ፡ ቦታ ፡ እንደ ፡ ያዘች ፡ በጥቅም ፡ ረገድ ፡ ያለው ፡ ቅርብ ፡ ግንኙነት ፡ ራሱ ፡ ያስረዳል ። በየጊዜው ፡ እያደገ ፡ ከሚሄደው ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ንግድ ፡ የሚበዛው ፡ ክፍል ፡ ወደ ፡ እንግሊዝ ፡ ግዛቶች ፡ ያመራል ። አብዛኛውንም ፡ የሚያካሂዱት ፡ ታላላቅ ፡ የንግድ ፡ ቤቶች ፡ የእንግሊዝ ፡ ናቸው ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ።

ያለፈው ፡ ጦርነት ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ባለፉት ፡ ዓመቶች ፡ ውስጥ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ኤኮኖሚ ፡ ከተጠበቀው ፡ ይበልጥ ፡ መስፋፋቱ ፤ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተነገረውን ፡ አረጋግጠ ፡ ይገኛል ። የኢትዮጵያ ፡ መገበያያ ፡ ገንዘብ ፡ ከአራት ፡ ዕጥፍ ፡ የበለጠ ፡ ሆኗል ። የመንግሥታችን ፡ ባንክ ፡ ተቀማጭ ፡ ገንዘብ ፡ በመቶ ፡ ሁለት ፡ ሺ ፡ ጨምሯል ። በውጭ ፡ አገር ፡ ያለን ፡ ገንዘብ ፡ ምንዛሪ ፡ እንደ ፡ መብዛቱ ፡ መጠን ፤ እንደዚሁም ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ጋራ ፡ ያለን ፡ ንግድ ፡ አራት ፡ ዕጥፍ ፡ ሆኗል ።

ኢትዮጵያ ፡ አዲስ ፡ በሆነ ፡ የሥራ ፡ ዘመን ፡ ውስጥ ፡ ስለምትገኝ ፤ ከማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ይበልጥ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የሥራ ፡ ክፍል ፡ ለመፈጸም ፡ በዚህ ፡ የሥራ ፡ እርምጃ ፡ የእንግሊዝ ፡ ካፒታልና ፡ እንዱስትሪ ፡ ተካፋይ ፡ እንዲሆን ፡ በጊዜው ፡ ገልጠነው ፡ የነበረው ፡ ምኞት ፡ አይለወጥም ፤ አሁንም ፡ ተካፋይ ፡ እንደሚሆን ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን ።

በሁለቱ ፡ አገሮች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ የወንድማማችነት ፡ መተሳሰብ ፡ ስንመለከት ፡ እጅግ ፡ ያጽናናናል ። የመላው ፡ ዓለም ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ጠቅላላ ፡ ማኅበር ፡ ባደራጀው ፡ የጎብረት ፡ ፕሮግራም ፡ ተካፋይ ፡ በመሆን ፤ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሙሉ ፡ እርዳታዋን ፡ አድርጋለች ። ይህ ፡ ታላቅ ፡ ግምት ፡ ሊሰጠው ፡

የሚገባ ፡ ሥራ ፡ ፍሬውን ፡ ያገኝ ፡ ዘንድ ፡ የእንግሊዝ ፡ ቤተ ፡ ክህነት ፡ ሰዎችና ፡ በተለየም ፡ ብፁዕ ፡ የካንተርበሪ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ እጅግ ፡ ክፍ ፡ ባለ ፡ ክርስቲያናዊ ፡ መሪነት ፡ ለደከሙት ፡ ድካም ፡ ምስጋና ፡ ይገባቸዋል ።

ሁለቱን ፡ አገሮች ፡ ያስተባበራቸው ፡ የጋራ ፡ ጥቅምና ፡ መሠረታዊ ፡ አሳብ ፡ በበለጠ ፡ እየበረታ ፡ የሚሄድበት ፡ ድርጅት ፡ እንዲገኝ ፡ አሳቢ ፡ የሆነችውን ፡ ኢትዮጵያን ፡ እውነተኛ ፡ የልብ ፡ ወዳጅ ፡ ናት ፡ ብላችሁ ፡ ለመቊጠር ፡ ትችላላችሁ ።

ለለንደን ፡ ከንቲባና ፡ ኮርፖሬሽን ፡ ጤና ፡ ጽዋዬን ፡ አነሣለሁ ።

433

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ጥቅምት ፡ ፭ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፻፯፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ዐርብ ፡ ማታ ፡ ከማታው ፡ በ፪ ፡ ሰዓት ፡ ለግርማዊት ፡ ንግሥት ፡ ኤልሳቤጥና ፡ ለልዑል ፡ የኤድንብራ ፡ መስፍን ፡ ክብር ፡ ሎንዶን ፡ ባለው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ኤምባሲያቸው ፡ ባደረጉት ፡ ታላቅ ፡ የራት ፡ ግብዣ ፡ ላይ ፡ ያደረጉት ፡ ንግግር ።

ግርማዊት ፡ ሆይ ።

የዛሬ ፡ ሠላሳ ፡ ዓመት ፡ የእንግሊዝን ፡ አገር ፡ መጀመሪያ ፡ በጐበኘሁበት ፡ ጊዜ ፡ ግርማዊት ፡ ንግሥት ፡ ገና ፡ በእግዚአብሔር ፡ ምሥጢራዊ ፡ አሳብ ፡ የሚመረጡ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ግርማዊት ፡ ንግሥትና ፡ የተወደዱ ፡ ኮንሶርዎን ፡ እንደ ፡ ዛሬ ፡ ማታ ፡ በደስታ ፡ ለማስተናገድ ፡ ይህን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ክብርና ፡ ዕድል ፡ አላገኘሁም ፡ ነበር ።

አባቴ ፡ ልዑል ፡ ራስ ፡ መኰንን ፡ ከዛሬ ፡ ፶ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ የቅድም ፡ አያትዎን ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ ለማክበር ፡ ወደ ፡ ታላቂቱ ፡ ብሪታንያ ፡ መጥተው ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፤ ለተወደደው ፡ አገርዎና ፡ እጅግ ፡ ከፍ ፡ ላለው ፡ ሕዝብዎ ፡ የነበራቸውን ፡ ታላቅ ፡ አድናቆት ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ አገራቸው ፡ ተመልሰው ፡ ነበር ። እኔም ፡ ራሴ ፡ የዛሬ ፡ ሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ይህን ፡ አገር ፡ ስጐበኝ ፡ በዚሁ ፡ መኰብኘቴ ፡ ጊዜ ፡ ታላቂ ፡ አያትዎ ፡ የአጼ ፡ ቴዎድሮስን ፡ ዘውድ ፡ በኔ ፡ አማካይነት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ እንዲመለስ ፡ ሲያደርጉ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ መንግሥትና ፡

ሕዝብ ፡ ላላቸው ፡ የልብ ፡ ወዳጅነት ፡ ዋና ፡ መግለጫ ፡ ምልክት ፡ ሆኖ ፡ የተቈጠረ ፡ ነው ።

ዛሬም ፡ ከእንግሊዝ ፡ ጋራ ፡ ላለን ፡ የወዳጅነትና ፡ የመልካም ፡ መግ ናኛ ፡ መሽጋገሪያ ፡ ግርማዊትነትዎ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፤ በዘመነ ፡ መንግሥትዎ ፡ የሁለቱ ፡ አገሮች ፡ ፖለቲካና ፡ ኤኮኖሚ ፡ በጋራ ፡ ጥቅም ፡ መሠረት ፡ በበለጠ ፡ አኳኋን ፡ እያደገ ፡ እንዲሄድ ፡ እተማመናለሁ ።

የእንግሊዝን ፡ አገር ፡ ከጐበኘሁ ፡ ወዲህ ፡ ባለፉት ፡ ሠላሳ ፡ ዓመ ቶች ፡ ውስጥ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ጎዘንን ፡ የጣሉ ፡ ብዙ ፡ ነገሮች ፡ ደርሰ ዋል ። አገራችንንና ፡ የተወደደውን ፡ ሕዝባችንን ፡ ጎዘንና ፡ መከራ ፡ ጐብኝተውታል ። ነገር ፡ ግን ፡ በዚሁ ፡ ዘመን ፡ ውስጥ ፡ ጎዘን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡[በታሪክ ፡ ውስጥ ፡ የክብር ፡ ቦታ ፡ የያዙ ፡ ታላላቅ ፡ ነገሮች ፡ ተፈጽመዋል ። እነዚሁም ፡ የእንግሊዝ ፡ ጀግኖች ፡ በአገራቸው ፡ መሬ ትና ፡ ደግሞ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ነፃነት ፡ ለማስመለስ ፡ በአገራችን ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ የፈጸሙዋቸው ፡ ክብር ፡ የመላባቸው ፡ ተጋድሎዎች ፡ ናቸው ።

ልዑል ፡ የግሎስተር ፡ መስፍን ፡ የዘውድ ፡ በዓላችንን ፡ ለማክበር ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ መጥተው ፡ ያደረጉልንን ፡ መጐብኘት ፡ በታላቅ ፡ ደስታ ፡ እናስታውሰዋለን ።

ዛሬ ፡ ግን ፡ የተወደዱትንና ፡ ጸጋ ፡ የመላባቸውን ፡ ንግሥት ፡ ከተወደዱ ፡ ልጎሶራቸው ፡ ከልዑል ፡ የኤድንብራ ፡ መስፍን ፡ ጋራ ፡ ለማ ስተናገድ ፡ ካገኘሁት ፡ ዕድል ፡ በላይ ፤ ቀደም ፡ አድርጌ ፡ በንግግሬ ፡ እንደ ጠቀስሁት ፡ ለጠቅላላው ፡ ዓለም ፡ ሰላምና ፡ ነፃነት ፡ ታላቅ ፡ ክብር ፡ ባለው ፡ አኳኋን ፡ እጅግ ፡ ከፍ ፡ ያለውን ፡ መሥዋዕትነትና ፡ ተጋድሎ ፡ ያደረጉትን ፡ በግርማዊትነትዎና ፡ በልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ መሪነት ፡ ሥር ፡ ሆነው ፡ የዚህን ፡ ታላቅና ፡ ታሪካዊ ፡ አገር ፡ ዕድል ፡ በእጃቸው ፡ ይያዙትን ፡ የእንግሊዝ ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ ጭምር ፡ ለማስተናገድ ፡ በመ ቻሌ ፡ ደስታዬ ፡ ታላቅ ፡ ነው ። እንደሌሎቹ ፡ ሁሉ ፡ ለትክክለኛው ፡ ፍርድና ፡ ለመላው ፡ ዓለም ፡ ነፃነት ፡ በመቆላለክ ፡ ጀግንነትና ፡ ቈራጥ ነት ፡ ያሳዩት ፡ የሰር ፡ ዊስተን ፡ ቸርችልና ፡ የተከበሩት ፡ የምስተር ፡ አን ቶኒ ፡ ኤድን ፡ ስም ፡ እንደማይሞት ፡ ሆኖ ፡ በታሪክ ፡ ተጽፎ ፡ ይኖራል ።

ምንም ፡ እንኳ ፡ የታሪኩ ፡ ዘመን ፡ ጎዘንና ፡ መሥዋዕትነትን ፡ የሥራ ፡ ፍሬንና ፡ ክብርን ፡ እያፈራረቀ ፡ ያስገኘ ፡ ቢሆን ፤ መጨረሻው ፡ ዘመን ፡ ብሩህና ፡ ታላቅ ፡ ተስፋ ፡ ያለው ፡ ለመሆኑ ፤ ጸጋ ፡ የተሰጣቸው ፡ የወጣቷ ፡ ንግሥት ፡ እጅግ ፡ ከፍ ፡ ባለው ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ መቀመጥ ፡ የሚበቃ ፡ ምልክት ፡ ነው ።

በታላቅ ፡ አክብሮትና ፡ አድናቆት ፡ ለምንመለከታቸው ፡ ለግርማ ዊት ፡ ንግሥት ፡ ጤና ፡ ጽዋችንን ፡ እናነሣለን ።

434

ጥቅምት ፡ ፭ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፲፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሰኞ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ከክብር ፡ ተከታዮቻቸው ፡ ጋራ ፡ ከአሉላ ፡ ቀን ፡ በፊት ፡ ከሎንዶን ፡ ወደ ፡ ባስ ፡ ከተማ ፡ ሄዱ ። በዚያም ፡ የባስ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሙሉ ፡ የክብር ፡ አቀባበልና ፡ የምሳ ፡ ግብዣ ፡ አደረጉላቸው ። ከንቲባው ፡ የከተማውን ፡ መክፈቻ ፡ ቍልፍ ፡ ሲያስረክባቸውና ፡ በግብዣውም ፡ ላይ ፡ የተነገሩት ፡ ቃሎች ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ።

ሀ) ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የባስ ፡ ከተማን ፡ የመክፈቻ ፡ ቍልፍ ፡ ከከንቲባው ፡ ሲቀ በሉ ፡ የተናገሩት ፡ አጭር ፡ ቃል ።

ጎዘኔን ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ቻልሁ ። እንዲሁም ፡ ሕዝቤን ፡ ወደ ፡ ነፃነትና ፡ የሥልጣኔ ፡ ጐዳና ፡ ለመምራት ፡ ብርታት ፡ ያገኘሁት ፡ ከእ ናንተ ፡ ነው ።

* * *

ለ) የባስ ፡ ከተማ ፡ ከንቲባ ፡ የምስተር ፡ ጋሎፕ ፡ ንግግር ።

እንደ ፡ ኤውሮፓ ፡ አቈጣጠር ፡ ከ፲፱፻፴፯ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ወዲህ ፡ ከከተማችን ፡ ተቀማጭ ፡ ሕዝቦች ፡ መካከል ፡ አንደኛው ፡ የሆኑት ፡ ግር ማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የዚችን ፡ ከተማ ፡ የክ ብር ፡ መክፈቻ ፡ ለመቀበልና ፡ ባለፉት ፡ ዘመናት ፡ በዚች ፡ ከተማ ፡ መዝ ገብ ፡ ላይ ፡ ሞያ ፡ ያለውን ፡ ስማቸውን ፡ በፈረሙት ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ ዝርዝር ፡ ውስጥ ፡ ለመግባት ፡ ዛሬ ፡ ተመልሰው ፡ በእኛ ፡ መካከል ፡ ተገ ኝተዋል ።

ግርማዊ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የንግሥታችን ፡ የክ ብር ፡ እንግዳ ፡ ሆነው ፡ በአፊሲዬል ፡ የመጐብኘት ፡ ፕሮግራማቸውን ፡

ከጨረሱ ፡ በኋላ ፡ ወዲያውኑ ፡ ወደ ፡ ባስ ፡ በመምጣታቸው ፡ ክብር ፡ ሲሰ
ማን ፡ እንዲሁም ፡ ዛሬ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ እኛ ፡ መካከል ፡ በመገኘታቸው ፡
ደስ ፡ ብሎናል ።

እንዲሁም ፡ ግርማዊት ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ለመምጣት ፡
ሳይቻላቸው ፡ መቅረቱን ፡ በመስማታችን ፡ ኀዘን ፡ ተሰምቶናል ። ለግ
ርማዊት ፡ እቴጌ ፡ ሰላምታችንን ፡ እያቀረብን ፡ ለወደፊቱ ፡ በቅርብ ፡
ጊዜ ፡ ሙሉ ፡ ጤና ፡ እንዲያገኙ ፡ እንመኝላቸዋለን ። ግርማዊ ፡
ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በዚች ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ በቂዩበት ፡ የስደት ፡ ጊዜ ፡
ውስጥ ፡ ያሳዩትን ፡ ጸጥታ ፡ ትዕግሥትና ፡ ሞገስ ፡ ረሽም ፡ ጊዜ ፡ አእ
ምሮዋችን ፡ አልሰረዘውም ። እንዲሁም ፡ ግርማዊነታቸው ፡ ትተዋቸው ፡
የሄዱት ፡ ብዙ ፡ ወዳጅነት ፡ የተመላባቸው ፡ ዝናዎች ፡ ከቶ ፡ አይረ
ሱንም ።

በግፍ ፡ ወረራ ፡ ጉዳት ፡ ከደረሰባቸው ፡ መካከል ፡ የመጀመሪያው ፡
የሆኑት ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በድል ፡ አድራጊነት ፡ ወደ ፡
መናገሻ ፡ ከተማቸው ፡ በገቡበት ፡ ቀን ፡ ታላቅ ፡ ደስታ ፡ ተሰምቶን ፡
ነበር ። የዚህን ፡ ዕለት ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ከቤተ ፡ መንግሥ
ታቸው ፡ ሆነው ፡ መሠረታውያንና ፡ እውነተኛ ፡ ቃሎች ፡ የሚገኙበት ፡
ንግግር ፡ ለሕዝባቸው ፡ ተናግረዋል ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ግርማዊነታቸው ፡ ካደረጉት ፡ ንግግር ፡ አንድ ፡
ቅጅ ፡ ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ አስቀምጬው ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ ይገኛል ።
ከዚሁ ፡ ንግግርዎ ፡ ውስጥ ፡ የመጨረሻውን ፡ ፓራግራፍ ፡ እንድጠቅስ ፡
ግርማዊነትዎ ፡ ይፈቅድልኝ ፡ ዘንድ ፡ አምናለሁ ።

ይኸውም ፡ ጥቅስ ፡ «ለክፉ ፡ ሥራ ፡ በክፋት ፡ ብድር ፡ አትመልሱ ፤
የጭካኔ ፡ ሥራዎችን ፡ ለመፈጸም ፡ አትመኙ» ፡ ሲሉ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡
ነገሥት ፡ ለሕዝቡ ፡ የሰጡት ፡ የምክር ፡ ቃል ፡ ነው ።

435

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ጥቅምት ፡ ፲ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፯፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ረቡዕ ፡ ከአኩለ ፡
ቀን ፡ በኋላ ፡ በኦክስፎርድ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የዶክተርነት ፡ ዲግሪ ፡ ተቀበሉ ።

በዚህም ፡ ጊዜ ፡ የዶክተር ፡ ኦፍ ፡ ሲቪል ፡ ሎው ፡ የማዕርግ ፡ ልብስ ፡ ለብሰው ፡ በሴልዶ
ንያን ፡ (በኬልቄዶናውያን) ፡ አዳራሽ ፡ በተሰናዳው ፡ የክብር ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተቀመጡ ፡
የዩኒቨርሲቲው ፡ ፕሬዚዳንትና ፡ አፈ ፡ ጉባኤ ፡ በላቲን ፡ ቋንቋ ፡ ንግግር ፡ አድርገው ፡ የዲፕሎ
ማውን ፡ ጽሑፍ ፡ በትንሽ ፡ ማኅደር ፡ አድርገው ፡ ለግርማዊነታቸው ፡ ሰጡ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡
የተደረጉትም ፡ ንግግሮች ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ።

ሀ) የዩኒቨርሲቲው ፡ ፕሬዚዴንት ፡ ንግግር ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ሲያይዝ ፡ ከመጣው ፡ መንግሥታዊ ፡ ሐረግ ፡
የሚወለዱትን ፡ በጦርነትና ፡ በሰላም ፡ ጊዜ ፡ ሞያዎችዎ ፡ የታወቁትን ፡
የንጉሥ ፡ ሰሎሞንን ፡ የጥበብና ፡ የጀግንነት ፡ ባህሎች ፡ የወረሱትን ፡ ግር
ማዊነትዎን ፡ የምቀበለው ፡ በታላቅ ፡ ክብር ፡ ነው ። ከአሁን ፡ ቀደም ፡
በዕድልዎ ፡ የደረሱትን ፡ ብዙ ፡ ተለዋዋጭ ፡ ነገሮች ፡ ዛሬ ፡ ስመለከ
ተው ፡ አገርዎ ፡ የግፍ ፡ ወረራ ፡ በደረሰበት ፡ ጊዜ ፡ የዛሬ ፡ ፲፰ ፡ ዓመት ፡
የሆነውን ፡ ሁኔታ ፡ መለስ ፡ ብዬ ፡ አስታውሳለሁ ።

በዚያ ፡ ዘመን ፡ ለአገርዎ ፡ ለመከራከርና ፡ የዓለም ፡ መንግሥታት ፡
ማኅበር ፡ አገርዎን ፡ ለመርዳት ፡ እንዲተባበር ፡ ራስዎ ፡ ጀኔባ ፡ ላይ ፡
ተገኝተው ፡ ያደረጉት ፡ የዲፕሎማቲክ ፡ ትግል ፡ የመላውን ፡ ዓለም ፡
ሕዝቦች ፡ መንፈስ ፡ ቀስቅሶ ፡ ነበር ።

በዚያ ፡ ሰዓት ፡ ንግግርዎም ፡ ውስጥ ፡ ዓለም ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነ
ውን ፡ ማናቸውንም ፡ ነገር ፡ ልሠራ ፡ ሕዝቤ ፡ ወራሪው ፡ ጠላት ፡ ከአገሩ ፡
እስኪወጣ ፡ ድረስ ፡ ወይም ፡ ሕዝቤ ፡ ራሱ ፡ እስኪያልቅ ፡ ድረስ ፡ መዋጋ
ቱን ፡ አያቋርጥም ፡ ብለው ፡ ነበር ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ መራራው ፡ የስደት ፡
ጊዜ ፡ ቀጠለ ። ነገር ፡ ግን ፡ ከፎ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ቀድሞ ፡ የተናገሩት ፡
የቁራጥነት ፡ ቃል ፡ ተፈጽሞ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ በድል ፡ አድራጊነት ፡
ወደ ፡ መናገሻ ፡ ከተማዎ ፡ ተመለሱ ። ግርማዊነትዎ ፡ ለነፃነት ፡ ካደረ
ጉት ፡ ትግል ፡ በስተቀር ፡ ሕገ ፡ መንግሥትንና ፡ የምክር ፡ ቤትን ፡ ለአ
ገርዎ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ አቋቋሙ ።

እንዲሁም ፡ በስምዎ ፡ የተሰየመ ፡ ዩኒቨርስቲ ፡ ኮሌጅ ፡ አቆሙ ። ይህ ፡ በጎ ፡ አድራጎትዎ ፡ አክስፎርድ ፡ ባለነው ፡ በእኛ ፡ ዘንድ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ግምት ፡ ተሰጥቶታል ።

ከዚህም ፡ በላይ ፡ ለሕዝብዎ ፡ መልካም ፡ አኗኗር ፡ የአገርዎን ፡ ሀብት ፡ ለማልማት ፡ ብዙ ፡ ተግባሮች ፡ ፈጽመዋል ። በስደትም ፡ ዘመንና ፡ አገርዎ ፡ ለጊዜው ፡ በጠላት ፡ ኀይል ፡ ሥር ፡ ወድቃ ፡ በነበረች በት ፡ ጊዜ ፡ አገራችን፡ግርማዊነትዎን ፡ በደስታ ፡ ለመቀበል ፡ አዲስ ፡ የመ መኪያ ፡ ምንጭ ፡ አግኝታ ፡ ነበር ። ዛሬም ፡ መልካሙ ፡ የብርሃን ፡ ጊዜ ፡ ሲመለስ ፡ ግርማዊነትዎን፡በተቻለ ፡ መጠን ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ክብር ፡ በመቀ በል ፡ ዙራት ፡ ሲሰማን ፡ ደግሞ ፡ በአንድ ፡ በኩልም ፡ የግርማዊነትዎ ፡ ወዳጅነት ፡ ያለመዛነፉን ፡ ምስጋና ፡ በተመላበት ፡ ልባችን ፡ እናስታው ሳለን ።

ለግርማዊነትዎና ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ መነን ፡ ረዥም ፡ ዕድሜ ፡ ይስጥልን ፤ የግርማዊነትዎ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ይለምልም ፤ ሕዝብዎም ፡ በሰላ ምና ፡ በብልጽግና ፡ የእግዚአብሔር ፡ በረከት ፡ ይድረሰው ።

* * *

ለ) የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ንግግር ።

ክቡር ፡ ሆይ ።

በአክስፎርድ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ከኒው ፡ ኮሌጅ * አሁን ፡ የተቀበልሁ ትን ፡ የሕግ ፡ ዐዋቂነት ፡ መዓርግ ፡ ከታላቅ ፡ ክብር ፡ እቄጥረዋለሁ ።

ይህ ፡ ታላቅ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ለእንግሊዝ ፡ ሕዝብ ፡ የዕውቀት ፡ እድገ ትና ፡ የፖለቲካ ፡ መሪዎች ፡ በማውጣት ፡ ያደረገው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ እርዳታ ፡ ተወዳዳሪ ፡ የሌለው ፡ በመሆኑ ፡ ዘርዝሮ ፡ መናገር ፡ አስፈላጊ ፡ አይደለም ።

የእንግሊዝ ፡ ሕዝብ ፡ ለዕውቀት ፡ እድገትና ፡ ለመንፈሳዊ ፡ ትምህ ርት ፡ ከሁሉ ፡ አብልጦ ፡ ታላቅ ፡ ዋጋ ፡ የሚሰጠው ፡ ለመሆኑና ፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ ላለው ፡ ጽኑ ፡ እምነት ፡ እነዚህ ፡ ሕንፃዎች ፡ ይመሰክራሉ ፤ ይህ ፡ ኮሌጅ ፡ በአክስፎርድ ፡ ከሚገኙት ፡ ከዋንታዊዎቹ ፡ አንዱ ፡ ሲሆን ፤ በዚ ያን ፡ ጊዜ ፡ አዲሱ ፡ ኮሌጅ ፡ ተብሎ ፡ መሰየሙ ፡ ከትውልድ ፡ ወደ ፡ ትው ልድ ፡ ሲተላለፍ ፡ ከመጣው ፡ ጥንታዊ ፡ ወግ ፡ ጋራ ፡ ተያይዞ ፡ የሚያስከ ብረው ፡ ነው ።

ይህ ፡ አገር ፡ ለክርስትና ፡ ሃይማኖትና ፡ ለነፃነት ፡ መሪ ፡ በመሆን ፡ አሁን ፡ ካለበት ፡ ደረጃ ፡ ለመድረስ ፡ የቻለው ፡ በዚህ ፡ በአክስፎርድና ፡ አክስፎርድን ፡ በመሰሉ ፡ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ከብዙ ፡ ዘመናት ፡ አንሥቶ ፡ በደረጃውና ፡ በቁየው ፡ የትምህርት ፡ ቅርስ ፡ መሆኑ ፡ የታወቀ ፡ነው ።

መሠረተ ፡ ጥልቅ ፡ የሆነውን ፡ ጥንታዊ ፡ ወግ ፡ በመጠበቅ ፡ በኢት ዮጵያና ፡ በአክስፎርድ ፡ መካከል ፡ ታላቅ ፡ ተመሳሳይነት ፡ ይገኛል ፤ ኢት ዮጵያ ፡ ዘወትር ፡ የነፃነትን፡መሠረትና፡የክርስትናን ፡ ሃይማኖት ፡ ጠብቃ ፡ የኖረች ፡ አገር ፡ ናት ። የዛሬ ፡ ሐያ ፡ ዓመት ፡ ግፈኛውን ፡ ወራሪ ፡ ብቻ ዋን ፡ እንድትከላከል ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ ለፈጸመችው ፡ ተጋድሎ ፡ ብርታ ትና ፡ ምሳሌ ፡ የሆናት ፡ በሔሮድቱስ ፡ ታሪክ ፡ ተጽፎ ፡ የሚገኘው ፡ ከዛሬ ፡ ሁለት ፡ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ የነበረው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ ጎይለኛው ፡ ካምቤሲስ ፡ በተባለው ፡ ንጉሥ ፡ ላይ ፡ የሠራው ፡ ሥራ ፡ ነው ፤ በክርስቶስ ፡ ያለንን ፡ እምነት ፡ በመጠበቅ ፡ ለክርስትና ፡ ሃይማ ኖት ፡ ስንከላከል ፡ የኖርነው፡ ከአራተኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ጀምሮ ፡ ነው ።

ባለንበት ፡ ዘመን ፡ ለኑሮዋችን ፡ መሠረት ፡ አድርገን ፡ የያዝነውን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ አሳብ ፡ ሁላችንም ፡ እያንዳንዳችን ፡ እንድንከላከልለትና ፡ እን ድንጠብቀው ፡ ያለንበት ፡ የጊዜው ፡ ሁኔታ ፡ ያስገድደናል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አሁን ፡ ያለንበት ፡ ዘመን ፡ ቶሎ ፡ ቶሎ ፡ ተለዋዋጭ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ እንደጊ ዜው ፡ አኳኋንና ፡ አስፈላጊነት ፡ መራመድ ፡ አለብን ፡ እንጂ ፡ በመሠረ ታዊ ፡ አሳብ ፡ ብቻ ፡ እየተመራን ፡ ለመኖር ፡ አይቻልም ፡ የሚል ፡ አስተ ያየት ፡ ተፈጥሯል ። እኔ ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ አስተያየት ፡ የምስማማ ፡ አይደ ለሁም ። ባለፉት ፡ አያሌ ፡ መቶ ፡ ዓመታት ፡ ለተደረጉት ፡ ጦርነቶችና ፡ ተጋድሎዎች ፡ መነሻ ፡ ለሆኑት ፡ ምክንያቶች ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ፍርድ ፡ ማመዛዘኛ ፡ የሚሆን ፡ የተጣራ ፡ ታሪክ፡ እስካሁን፡ አልተገኘም ። በአሁኑ ፡ ትውልድ ፡ ላይ ፡ ለተደረጉት ፡ ጦርነቶችና ፡ ለደረሱበት ፡ መከራዎች ፡ ግን ፡ ምክንያቶቹ ፡ ምን ፡ እንደ፡ሆኑ ፡ ታውቀዋል ። እንደዚሁም ፡ በዘመ ናችን ፡ በሕገ ፡ ውጡነት ፡ የተሠሩ ፡ የግፍ ፡ ሥራዎች ፡ ሁሉ ፡ ቅጣታቸ ውን ፡ በአጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ተቀብለዋል ። በዱሮዎቹ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ መፈጸሙን ፡ የሚያስረዳ ፡ ታሪክ ፡ አልተገኘለትም ።